# በገንዘብ ሚኒስቴር

## የቻናል አንድ ፕሮግራሞች  ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት

**በአዳዲስ ወረዳዎች**

# የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም አተገባበር ማኑዋል

**ነሐሴ 2014**
**አዲስ አበባ**

# ማውጫ


የአህጽሮተ ቃላት ዝርዝር ........ 3

1. መግቢያ ........ 4

2. ዓላማ ........ 5

3. ዋና ዋና ተግባራት ........ 6

4. የአፈፃፀም ስልቶች ........ 7

4.1. የወረዳና ቀበሌ መረጣ ሂደት፤ ........ 7

4.2. ስራው የሚሸፍናቸው የአገልግሎት ሴክተሮች ........ 7

4.3. የአቅም ግንባታ ድጋፍ ........ 8

4.4. ከምክርቤቶች ጋር ስለሚሰሩ ስራዎች፤ ........ 8

4.5. ከማህበረሰብ በቀል የዜጎች ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ........ 9

4.6. የቡድንና የገፅ ለገፅ ስብሰባዎችን ማመቻቸት ........ 10

4.7. በማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ የመሰረታዊ አገልግሎት ዘርፎች (Basic service sectors) ሚና ........ 10

4.8. ለማህበራዊ ተጠያቂነት ትግበራ የአካባቢ ሚዲያዎችን መጠቀም ........ 11

4.9. የመንግስት መሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ግምገማ መስፈርቶች ........ 12

5. ክትትልና ግምገማ ........ 13

# የአህጽሮተ ቃላት ዝርዝር

| | |
|---|---|
| **ACSO** | Authority for Civil Society Organizations (የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን |
| **CBOs** | Community Based organizations (የማህበረሰብ ምስርት ተቋማት) |
| **ESAP (ኢሳፕ)** | Ethiopian Social Accountability Program (የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም) |
| **IDA (አይ.ዲ.ኤ)** | International Development Association WBG (አለም አቀፍ የልማት ማህበር በዓለም ባንክ) |
| **JAP** | Joint Action Plan (የጋራ ድርጊት መርሃ ግብር) |
| **MA** | Management Agency( ማናጅመንት ኤጄንሲ) |
| **MDGs** | Millennium Development Goals ( የሚሊዬኒየም የልማት ግቦች) |
| **MBOs** | Mass Based Organizations (የብዙሃን ማህበራት) |
| **PSTU (ወተመህ)** | Parent Student Teacher Union (የወላጅ ተማሪ መምህር ህብረት) |
| **SA** | Social Accountability (ማህበራዊ ተጠያዊነት) |
| **SACs** | Social Accountability Committees (የማህበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎች) |
| **SAPs** | Social Accountability Platforms (ማህበራዊ ተጥያቂነት መድረኮች) |
| **SDGs** | Sustainable Development Goals ( ዘላቂ የልማት ግቦች) |

## 1. መግቢያ

ተጠያቂነት (Accountability) በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ ውሳኔ ሰጪ አካላት ለሚወስኑትም ውሳኔ ሆነ ለሚያከናውኑት ስራ ኃላፊነትን የሚወስዱበት የአሰራር ሥርዓት ነው። በተለይ በህዝብ የተመረጡ የመንግስት ባለ ስልጣናትና ኃላፊዎች የህዝቡን ፍላጎትና መብት የማስከበር ኃላፊነትና አደራ ስለተጣለባቸው በመንግስታዊ ህጎችና ሰነዶች ላይ ተጠያቂነትን እንደ አንድ መሰረታዊ የመንግስት አሰራር መርህ መቀበል የተለመደና ተቀባይነት ያለው ዓለማቀፋዊ አሰራር ነው።

ማህበራዊ ተጠያቂነት ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት የአገልግሎት አቅራቢ አካላትንና ውሳኔ ሰጪ የመንግስት ኃላፊዎችን ስለሚሰጡት ማንኛውም አይነት የህዝብ አገልግሎት አርኪነት፣ ፍትሀዊነትና ተደራሽነት ጥያቄ የሚያቀርቡትና በመፍትሄ አሰጣጡም ላይ በቀጥታ የሚሳተፉበት የአሰራር ዘዴ ነው።

ማህበራዊ ተጠያቂነት (Social Accountability) በርካታ ጥቅሞች አሉት። ከነዚህም መካከል አንደኛው የመንግስት አሰራርን ግልጽ፣ ፍትሃዊ፣ አካታችና ከሙስናና መድሎ የፀዳ በማድረግ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን የሚረዳ መሆኑ ሲሆን፤ ሁለተኛው ዜጎች መብትና ግዴታቸውን በሚገባ ተገንዝበው በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ በቀጥታ እንዲሳተፉና ከውሳኔ ሰጪ የመንግስት አካላት ጋር በታቀደ፤በተደራጀና በመግባባት ላይ በተመሰረተ መንገድ በመመካከር ለልማት ችግሮች የጋራ መፍትሄ የሚሹበት አሰራር መሆኑ ነው። (SA as a mechanism that fosters organized, predictable and constructive dialogue between citizens and government and paves a way for joint problem solving development action) ከዚህ በተጨማሪም ማህበራዊ ተጠያቂነት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት (በተለይም እኤአ ከ2004 ዓ ም ጀምሮ) በአለም አቀፍ ደረጃ ለድህነት ቅነሳ፣ ለሙስናና ብልሹ አስራሮች መወገድ፣ ለመስረታዊ የህዝብ አገልግሎቶች መሻሻልና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለተጣሉት የልማት ግቦች (MDGs & SDGs) መሳካት በመንግስታትና ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች ተቀባይነትና ትኩረት አግኝቶ በስራ ላይ የዋለ አሰራር ነው።

በኢትዮጵያ የመንግስትን አሰራር ለህዝብ ግልጽ፤ተጠያቂና አሳታፊ የሚያደርግ ምቹ የሆነ ህገ-መንግስታዊ መሠረት አለ፡ በዚህ ረገድ የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 12፡ 1) የመንግስት አሰራር ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት 2) ማንኛውም ሃላፊና የህዝብ ተመራጭ ሃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል በማለት ሲደነግግ፣ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 4 መ ደግሞ፤ 'ህዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ስልጣን ይሰጣል' ማለቱን በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል።

የኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም (ኢሳፕ) በአምስቱ መሰረታዊ አገልግሎት ዘርፎች ማለትም፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በውሃ፣ በግብርና እና በገጠር መንገድ አገልግሎቶች፤ የማህበራዊ ተጠያቂነት ስልቶችን እና አሰራሮችን (SA Tools and Mechanisms) በመጠቀም የመንግስት አገልግሎት አስጣጥን ለማሻሻል ያለመ ነው። ፕሮግራሙ በአሁኑ ወቅት በሶስተኛው ምእራፍ ላይ

የሚገኝ ሲሆን በሁለት የገንዘብ ምንጮች (funding streams) በመጠቀም ይተገበራል። አንደኛው በዓለም ባንክ አስተባባሪነት እና በለጋሽ የልማት አጋር ድርጀቶች ድጋፍ የማኔጅመንት ኤጀንሲው ከሲቪል ማህበራት ጋር በመሆን የሚተገብሩት (Multi Donor Trust Fund) ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ በዓለም ባንክ (IDA) እርዳታና ድጋፍ፤ በገንዘብ ሚኒስቴር እና በክልል የፋይናንስ ቢሮዎች የሚመራ በመሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር መስሪያቤቶች ውስጥ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ለማስረፅና አሰራሩንም በሂደት ዘለቄታዊና ተቋማዊ ለማድረግ የሚሰራ ነው።

ኢሳፕ-አይ.ዲ.ኤ(ESAP-IDA) በዋነኝነት ፕሮግራሙን አግባብ ላላቸው የፌደራልና የክልል ባለድርሻ አካላት ማስተዋወቅን ጨምሮ የአቅም ግንባታና የመሰናዶ ስራዎች የተከናወኑበትን የ2014 የመጀመሪያ አመት ስራውን ያጠናቀቀ ሲሆን በአሁኑ ወቅትም ፕሮጅክቱን ወደ ሙሉ ትግበራ ለማሸጋገር የ2015 ዓ.ም. እቅድና በጀቱን በማጸደቅ ወደስራ ገብቷል።

በእቅዱ መሰረት በ2015 የበጀት ዘመን ትኩረት ከሚደረግባቸው ዋና ዋና ስራዎች መካከል፤

ሀ) ቀደም ሲል በስራ ላይ የቆዩ 50 የኢሳፕ ወረዳዎችን ከማኔጂመንት ኤጄንሲው በታህሳስ ወር 2015 በመረከብ የማህበራዊ ተጠያቂነት አሰራርን ማስቀጠል (Implementing & Sustaining SA in 50 ESAP Woredas to be handed over by the MA)፣

ለ) በስራው ለሚሳትፉ የመንግስት መሰረታዊ አገልግሎት ሰጪ አካላት፤ ለክልልና ወረዳ ምክር ቤት አባላትና የሴክተር መ/ቤቶች ፤ ስለማህበራዊ ተጠያቂነት አሰራር፤ የአቅም ግንባታ ስልጠናና የአሰራር ሰርዓት ድጋፍ (SA skill & operational system development support) መስጠትና፤

ሐ) መደበኛ የፕሮጀክት ማኔጅመንትና በጀት አስተዳደር ስራዎችን በማከናወን፣ የስራውን ውጤታማነት በተዘረጋው የክትትልና ግምግማ አስራር መሰረት ማረጋገጥ፤

ይገኙበታል።

በ2015 የበጀት አመት በመንግስትና ተገልጋዩ ህብረተስብ ቀጥተኛ ተሳተፎና ትብብር በተመረጡ አዳዲስ ወረዳዎች (Non-ESAP Woredas) የሚከናወኑ የማህበራዊ ተጠያቂነት ስራዎችም ታቅደዋል። በእነዚህ አዳዲሰ ወረዳዎች የሚተገበረውን የማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ ለማስፈጸም እንዲረዳም፤ የሚከተለው የአተገባበር ማኑዋል ተዘጋጅቷል።

## 2. ዓላማ

ይህ የአተገባበር ማኑዋል ሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም፣

ሀ) በአስር ክልሎች እና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች በተመረጡ ጥቂት ወረዳዎች የማህበራዊ ተጠያቂነትን አሰራር በማስጀመር በየደረጃው የሚገኙ የመንግስት ባለድርሻ አካላትን በስራው በቀጥታ በማሳተፍ፤ ተገቢውን ልምድና ተሞክሮ እንዲያገኙ ለማድረግ፤ (Provide

public service stake holders with hands-on experience on SA implementation)

ለ) በዘጠኝ ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች በተካሄዱ የኢሳፕ አይዲኤ ፕሮግራም ማስተዋወቂያ መርሃግብሮች እና በቅርቡ በተከናወነው የዳሰሳ ጥናት ወቅት በክልል የምክር ቤት አባላት፣ የአገልግሎት ስጪ ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት ዘንድ ፕሮግራሙን ለማገዝ ለታየው ተነሳሽነት እና ፍላጎት ተጨባጭ ምላሽ ለመስጠት (To keep the SA momentum going).

ናቸው።

## 3. ዋና ዋና ተግባራት

ቀደም ሲል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጸድቆ በሰራ ላይ የዋለውን የማህበራዊ ተጠያቂነት የትግበራ መመሪያን (SA Implementation Guide: COPCD March, 2022) መሰረት በማድረግ የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች፣ የክልል የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ተጠሪዎችና ለሰራው የተመደቡ የወረዳ ፋይናንስ ጽ/ቤት ባለሙያዎች የኢሳፕ-አይ.ዲ.ኤ ስራን በአዲስ ወረዳዎች በሚከተለው መልኩ ያከናውናሉ።[1]

- መሰረታዊ የመንግስት አገልግሎቶች ተገልጋዩን ህብረተስብ ባሳተፈና ተጠያቂነትን ባረጋገጠ መልኩ ለማቅረብ እንዲቻል የህዝብን ፍላጎትና የመንግስትን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ለመለየት ከሴክተር ቢሮዎች ጋር የምክክር ስብሰባዎችን ማካሄድ፣
- በተመረጡ መመዘኛዎች መሰረት ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር በሚደረግ ምክክር ሰራው የሚተገበርባቸውን ወረዳዎችን መምረጥ፣
- በተመረጡ ወረዳዎች ውስጥ የመሰረታዊ አገልግሎት basic service standards ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ማሳወቅ፣
- በተመረጡ ወረዳዎች ከሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር መስሪያ ቤቶችና፤ ህዝባዊ ማህበራት አንዲሁም፤ አገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎች ተወካዮች ጋር (ለጉዳት ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ (inclusive of vulnerable social groups)) በቂና አሳታፊ ውይይት በማድረግ በ5ቱ መሰረታዊ አገልገሎት ዘርፎች ማእቀፍ ውስጥ በአሁኑ ወቅት የሚታዩ የመሰረታዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችንና የተገልጋዩን ህብረተሰብ ተቀዳሚ ፍላጎቶች መለየት፣
- ስራው ለሚመለከታቸው የመንግስት ባለድርሻ አካላት፣ ማለትም ለወረዳ አስተዳደር፣ ምክር ቤት እና ሴክተር ኃላፊዎች የማህበራዊ ተጠያቂነት ግንዛቤ ማስጨበጫና አቅም ግንባታ ስልጠና አዘጋጅቶ መስጠት፣

[1] ይህ ዝርዝር ለስራ መነሻ ሆኖ እንዲያገለግል በሚል የተዘጋጀ ሲሆን ፤ በሂደት እንዳሰፈላጊነቱና እንደየክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ **አላማውን ጠብቆ**፣ ሊሻሻል፤ሊሰፋ ሊጠብ የሚችል ነዉ። አዳዲስ ለውጦች ሲያስፈልጉ የክልል የፋይናንስ ቢሮዎች፤የሚኒስቴር መ/ቤቱን ማማከር ይጠበቅባቸዋል። ይህም የሚደረገው የሰራውን ጥራት ለማረጋገጥና በጎ ልምዶችን ለሌሎች ክልሎች ለማካፈል ጠቃሚ በመሆኑነው።

- የወረዳ የፋይናንስ ፅ/ቤት ሰራተኞችን በማህበራዊ ተጠያቂነት አላማዎች፣ ስልቶችና ልምዶች፣ የማህበራዊ ተጠያቂነት የትግበራ መመሪያ እንዲሁም የ2015 ዓ.ም. እቅድ እና በጀት ላይ ማሰልጠን፣
- የማህበራዊ ተጠያቂነት የጋራ ውይይቶች አመቻቾችን (Facilitators of interface meetings) መምረጥ እና ማሰልጠን
- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የማህበራዊ ተጠቂነት ቡድን ከተለያዩ ለስራው አግባብነት ካላቸው ድርጅቶችና ባለሙያዎች ጋር በመሆን በሚያዘጋጀው ስልጠናና በኢሳፕ ልምድ ላይ በመመስረት የማህበራዊ ተጠያቂነት ኡደትን መተግበር፣ (Implement the SA cycle based on ESAP's experience)
- በመስክ ምልከታ የታገዘ መደበኛ የፕሮጀክት አቅድ አፈጻጸም ክትትል ማድረግና፤ የወረዳ የፋይናንስ ፅ/ቤቶች ለክልል የ ፋይናንስ ቢሮዎች፤ የክልል ቢሮዎቹም ለገንዘብ ሚ/ር ቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ወቅታዊና መደበኛ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ማቅረብ፤

ናቸው።

# 4. የአፈፃፀም ስልቶች

## 4.1. የወረዳና ቀበሌ መረጣ ሂደት፤

- ማህበራዊ ተጠያቂነትን ለመተግበር በአይ.ዲ.ኤ. በጀት የሚሸፈን፤ ከየክልሉ **አንድ ወረዳ** ብቻ ይመረጣል፤
- የወረዳ መምርጫ መስፈርት የገንዘብ ሚ/ር ቻናል አንድ ፕሮገራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት ከክልል የፋይናንስ ቢሮዎች ጋር በቅርቡ ባዘጋጀው የ2014 እቅድ አፈፃፀም ግምገማና የ2015 እቅድ ዝግጅት አውደጥናት ላይ በተደረገው ውይይትና በተደረሰው መግባባት መሰረት፤ በክልሉ **በንጽጽር፤ የተሻለ የስራ አፈጻጸም ላላቸውና አመቺ የትራንስፖርት አገልገሎት** ላላቸው ወረዳዎች ቅድሚያ በመስጠት ይፈጸማል[2]።
- የወረዳ ምርጫው እንደተጠናቀቀ፤ ከወረዳው አስተዳደሩና በስራው ከሚሳተፉ የሴክተር መ/ቤቶች ጋር እንዲሁም በስራው ለመሳተፍ አግባብነት ካላቸው የወረዳው ህዝባዊ ማህበራት ተወካዮች ጋር (ለተለያየ ጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የማህረሰብ ክፍሎችን፤ ማለትም የሴቶችን፣ አረጋዊያንና አካለጉዳተኞችን ተወካዮችን ባካተተ መልኩ)፤ በሚደረግ ግልጽና በመግባባት ላይ የተመሰረተ ውይይት በወረዳው ዋና ከተማ ውስጥ፤ ወይም አቅራቢያ በሚገኝ አንድ **የከተማና አንድ የገጠር ቀበሌ** ፤በድምሩ በሁለት ቀበሌዎች የሚከናወን ይሆናል።

## 4.2. ስራው የሚሸፍናቸው የአገልግሎት ሴክተሮች

- በ5ቱ መሰረታዊ አገልገሎት ዘርፎች ማእቀፍ ውስጥ አዲስ የተመሰረቱ የዜጎች ቡድኖች/መድረኮች ከየሴክተሩ፣ ከአንድ ሴክተር ወይም የተለያዩ ሴክተሮችን የሚመለከቱ (multi-sectorial) ለህዝብ አንገብጋቢ የሆኑ የአገልግሎት ጉዳዮችንና ችግሮችን (service user priority issues and problems) ይለያሉ፤

[2] *ይህም ያስፈለገበት ምክንያት ፤ስራው ለመጀመሪ ጊዜ በመንግስት አስተባባሪነት የሚከናውን እንደመሆኑ በተቻለ መጠን በስራው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያደርጉ የሚችሉ ውጫዊ ምክንያኞቶችን በመቀነስ ስራው ስኬታማ እንዲሆን ለማድረግ ነው።*

- በወረዳ ደረጃ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ  የመሰረታዊ አገልግሎት ዘርፎች (basic service sectors) የማህበራዊ ተጠያቂነትን ስራ ለማስጀመር የሚወሰነው፡ ከአግልግሎት ተቀባዩ ህብረተሰብ ተወካዮችና፤ከሴክተር ቢሮዎች ጋር ውይይት በማድረግ  ስለ ዜጎች አንገብጋቢ ፍላጎትና የክልሉ ቅደም ተከተሎች ላይ ያላቸውን ሃሳብ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፣
- አስቀድመው፤ በራሳቸው ተነሳሽነት ማህበራዊ ተጠያቂነትን እየተገበሩ ያሉ ሲክተሮች (ለምሳሌ ጤና ቢሮዎች) በያዙት ህዝቡን በአገልግሎት አሰጣጥ ሰራ የማሳተፍ ስራ የተለየ የፕሮግራም ድጋፍ ይደረግላቸዋል[3]።

## 4.3. የአቅም ግንባታ ድጋፍ

- የክልል የፋይናንስ ቢሮዎችና የማህበራዊ ተጠያቂነት ባለሙያዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማህበራዊ ተጠያቂነት ቡድን ሙያዊ ድጋፍ በመታገዝ፤ በክልልና ወረዳ ደረጃ የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የማህበራዊ ተጠያቂነት ዑደት ትግበራ (SA cycle implementation) ላይ  ወደ ስራ የሚያስገባ ስልጠና ያዘጋጃሉ። ስልጠናውም ቀደም ሲል ተመሳሳይ ስራ በሰሩ አግባብነት ያላቸው ድርጅቶች በሚደረግ፤ የመስክ ጉብኝትና የልምድ ልውውጥ እንዲታገዝ ይደረጋል።
- ሁሉም ስልጠናዎች የሰልጣኝ ድርጅቶችን ፍላጎትና የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ የሚዘጋጁ ሲሆን፣ በስልጠናዎቹ መጨረሻም ቀጣይ እንቅስቃሴዎች፣ ግልፅ እና ሊተገበሩ የሚችሉ ግቦች፣ እንዲሁም የስራ ድርሻዎች እና የትግበራ የጊዜ ሰሌዳዎች ይቀመጣሉ። ተፈጻሚነታቸውም በየጊዜው በሚደረግ የመስክ ክትትልና ግምገማ ይረጋገጣል።
- የመሰረታዊ አገልግሎት ሴክተሮች ማህበራዊ ተጠያቂነትን ደረጃ በደረጃ የእለት ተእለት ስራቸው አካል እንዲያደርጉት ለማስቻል፤ (to make it part of their daily routine) የአሰራር ስርዓት ዝግጅት ድጋፍ (operational system capacity support) ይደረግላቸዋል፣ ይህም  የማህበራዊ ተጠያቂነት ማንዋሎች፣ ቅጾች፣ መመሪያዎች እና የመሳሰሉትን ዝግጅትንና ትግበራን ያካትታል።

## 4.4. ከምክርቤቶች ጋር ስለሚሰሩ ስራዎች፤

- የወረዳና የክልል ም/ቤቶች፣አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከዜጎች ለሚቀርብላቸው የአገልግሎት ጥያቄዎች እና ፍላጎቶች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ መስጠታቸውን የማረጋገጥ እና የመቆጣጠር ህጋዊ ስልጣን ስላላቸው ኢሳፕ አይ.ዲ.ኤ. ከእነዚህ አካላት ጋር  የቅርብ ድጋፍ በመስጠትና በትብብር ይሰራል፤
- ከምክር ቤት አካላትና አባላት ጋር የሚሰሩ በርካታ የማስፈጸምና የአቅም ግንባታ ስራዎች በፕሮጅክት ሰነዱና በኢሳፕ አይ.ዲ.ኤ. የ2015 ዘመን እቅድና በጀት መሰረት የሚከናወኑ ይሆናል።
- የወረዳ ምክር ቤት አካላትና አመራር አባላት የአገግሎት አሰጣጥ ግምገማው (service assessment) እንዲሁም የጋራ የድርጊት መርሃ ግብር (JAP) ቀረፃው ክፍት፣ ነጻ እና በማስረጃ የተደገፈ  (open, free and evidence based) መሆኑን እንዲያረጋግጡና ፤ የመንግስት እቅድ  እና በጀት ላይ ውሳኔ  ሲሰጡ በጋራ የድርጊት መርሃ ግብር  (JAP)

[3] ኢሳፕ አይ.ዲ.ኤ. በአሁኑ ወቅት የጀመረውን በጤናው ዘርፍ  የማህበራዊ ተጠቂነት አሰራሮችን በመጠቀም አግለግሎቱን ለማሻሻል በመደረግ ላይ ያለውን ጥረት ለማገዝ የሚያደርገውን ከግምት ውስጥ በማስገባት፤

የተቀመጡ የህዝብ ፍላጎቶችን እንዲካተቱ በፕሮጀክቱ ተገቢ የቴክኒክ ድጋፍና አገዛ ይደረግላቸዋል።

- የምክር ቤት አባላት  የመስክ ጉብኝት በማድረግ ታች ወርደው ምን እየተሰራ እንዳለ የመገምገምና ከህዝቡ (ከአገልግሎት ተጠቃሚው) ግብረመልስ የማግኘት ሃላፊነታቸውን መወጣት እንዲችሉ ፍላጎታቸውንና የሰራ ቅደም ተከተላቸውን (Needs and priorities) መነሻ ያደረገ ሙያዊ እገዛ  ይደረግላቸዋል።
- ለወረዳ ምክር ቤቶች የሚሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ፤ ለክትትልና ግምገማ ስራ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የአስራር ዘዴዎችንና ቅጾችን እንዳስፈላጊነቱ ማዘጋጀትንና በስራ ላይ ለማዋል ምክር ቤቶቹ የሚያደርጓቸውን ጥረቶችን ማገዝን ያካትታል።

## 4.5. ከማህበረሰብ በቀል የዜጎች ተቋማት ጋር በትብብር መስራት

- በየአካባቢው ያሉ የማህበረሰብ ምስርት ተቋማት (CBOs)፣ የብዙሃን ማህበራት (MBOs) እንዲሁም የሙያ ማህበራት በአገልግሎት ተጠቃሚዎች በኩል ያሉ የፕሮግራሙ ባለቤቶች ናቸው። ከብዙ ሀገሮች ልምድ እንደታየው፤ ያለ አገልገሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብ ሁነኛ ባለቤትነትና፤ ቀጥተኛ ተሳትፎ፤ ማንኛውም የማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ (የቱንም ያህል በመንግስትና ለጋሽ ድርጅቶች ቀና ትብብርና ድጋፍ ቢታገዝ) ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት አይችልም።
- እዚህ ላይ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ፤ አገልግሎት ተቀባዩን ህብረተሰብ ፍላጎት በትክክል ሊረዱና፤ ተረድተውም የህዝቡን ጥያቄዎች በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍና ሳያመነቱ ለመንግስት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ኃላፊዎችና አግባብነት ላላቸው የወረዳና የክልል ውሳኔ ሰጪ አካላት፤ ማቅረብ የሚችሉትን የህዝብ ባለደርሻ አካላትን የመለየት ተግባር ነው። በልምድ አንደታየው አንዲህ አይነቱ መንግሥትን ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ተጠያቂ የማድረግና የመሞገት ስራ ከፍትኛ ፍላጎት፤ አቅምና የህዝብን አመኔታና ውክልናን የሚጠይቅ፤ በተጨማሪም የረዥም ጊዜና ተከታታይ አቅም ግንባታ የሚጠይቅ ስራ ነው።
- በእስከዛሬው የኢትዮጵያ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም (ESAP) ልምድ አንደታየው በፕሮጀክቱ በተለያየ ጊዜ የተቋቋሙት የማህበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎች (SACs) **ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም** ከፍተኛ ድርሻ ተጫውተዋል። ህዝቡ መብትና ግዴታውን በሚገባ ተገንዝቦ፤ ከመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋርም ስለፍላጎቱ  በግልጽ አንዲወያይ በማስቻልና፤ በመማሪያ መድረክነትም አገልግለዋል።
- አሁን ኢሳፕ በሚገኝበት የልምድና አድገት ደረጃ፤ በተለይም ከኢሳፕ አይ.ዲ.ኤ የወቅቱ አላማና ተልእኮ፤ ማለትም የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥን ስራ በዘለቄታው፣ ግልጽ፣ ፍትሃዊና **ምላሽ ሰጪ (responsive)** የማድረጉ ስራ፣ ከፕሮጀክት አሰራር ወደ ተቋማዊ አሰራር መሸጋገርን ይጠይቃል። ይህን ስራ በተጨማሪ የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይወጣሉ ተብለው የሚታሰቡት የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመወከልና **ህዝቡ ውስጥ ሁነኛ መሰረት ይዘው በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት ህዝባዊ ማህበራት ናቸው።** ከእነዚህ ባለድርሻዎች መካከል፤ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት፣ የውሃና ፍሳሽ ኮሚቴዎች፣ ወተመህ፣ የወጣት ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የእድር ዩኒየኖች፣የአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ማህበራት፤በግምባር ቀደምትነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።
- አዲሱ አሰራር  በአስካሁኑ ሂደት ከፍተኛ አገልግሎት የሰጡ የማህበራዊ ተጠያቂነት ኮሚቴዎች (SACs) የበለጠ ጥልቀትና ህዝባዊ መሰረት በመስጠት ወደ ማህበራዊ ተጥያቂነት ዘላቂ መድረኮች (Social Accountability Platforms/SAPs) መቀየርን

ይጠይቃል። የነዚህ የህዝብ ተሳትፎ መደረኮች አይነተኛ ባህሪ፤ የሚወክሏቸው የማህረሰብ ክፍል ካላቸውና የአካባቢ ህዝባዊ መሰረትና ተጠያቂነት ካላቸው ማህበራት የሚውጣጡና በዚህም የተነሳ የአገልገሎት አሰጣጡን ግልጽነት፤ ተደራሽነትና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ ከመንግስት አካላት የሚጠበቀውን ምላሽ ስጪ አሰራር በመጠየቅ፤ በማስረጃ በማቅረብና፤ ውሳኔዎችን ተከታትሎ በማስፈጸም የተሻለ አደረጃጀትና ቁመና ሊኖራቸው የሚችል መሆኑ ነው። ስያሜውም ለመነሻ የሚያገልግል ሆኖ በሂደት አየታየ አንዳስፈላጊነቱ ሊሻሻል የሚችል መሆኑ ታሳቢ ተደርጓል።

- እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ማህበራት በተወካዮቻቸው አማካኝነት በማህበራዊ ተጠያቂነት ሂደቱ ውስጥ በመሳተፍ የሚወክሏቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ፍላጎት እንዲንፀባረቅ ያደርጋሉ። ከመንግስት ሴክተር ውሳኔ ሰጪ አካላት ጋር በሚያደርጉት ውይይትም በተለያዩ እርከኖች (በወረዳና ክልል) ያሉ ማህበራት ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባል።
- ከሃገር በቀል የሲቪክ ማህበራቱ ጋር የሚከናወነውን የማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ በማስተባበሩ ረገድ፤ በአሁኑ ወቅት ከኢሳፕ አይዲኤ ጋር በትብብር አየሰራ የሚገኘው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን (ACSO) ጠቃሚ ሚና የሚኖረው ሲሆን ይህም በሚ/ር መስሪያ ቤቱ የቻነል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬትና በክልል የፋይናንስ ቢሮዎች በዝርዝር ተለይቶና ታቅዶ ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር በትብብር የሚከናወን ይሆናል።

## 4.6. የቡድንና የገፅ ለገፅ ስብሰባዎችን ማመቻቸት (Facilitation of Focus Group Discussions and Interface Meetings)

- በልምድ አንደታየው፣ በመንግስት የመሰረታዊ አገልግሎት ተቋማትና በተገልጋይ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የሚደረጉ የአገልግሎት አሰጣጥ ግምገማዎችና ውይይቶች ነፃና ገለልተኛ በሆኑ ባለሙያዎችና አወያዮች ሲመሩ፤ ህዘቡ በግልጽና ያለ ምንም ማመንታት ሀሳቡን በነጻነት ለማቅረብና አገልግሎት የማግኘት ህጋዊ መብቱን በሚገባ ለመጠቀም ያስችለዋል። የሂደቱ ተአማኒ መሆንም ለሚቀርቡት ጥያቄዎችና ለሚደረስባቸው ውሳኔዎች በመንግስት ውሳኔ ሰጪ የበላይ አካላትና፤ ተባባሪ የልማት አጋሮች በኩል ተቀባይነትና ወቅታዊ ምላሽ የማግኘት፤ ገንቢ አስተዋጽዎ ይናረዋል።
- በዚህ መሰረት በየወረዳው/ክልሉ ልምድ እና ችሎታ ያላቸው እንዲሁም በጎ ፍቃደኛ የሆኑ አመቻቾችን በመለየትና ፤በመመልመል ስለ ስራቸው በቂ ግንዛቤና ስልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፤
- የሚመረጡት አመቻቾች የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ፣ ባህል እና ቋንቋ የሚያውቁ እና **በህዝብና በመንግስት በኩል አመኔታ እና ተቀባይነት** ያላቸው ቢሆኑ ይመረጣል።
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በዚህ በኩል ልምድ ያላቸውን የሲቪክ ማህበራትን የመለየትና በስራው በፈቃደኝነት አንዲሰማሩ በማበረታታት ድጋፍ ሲያደርግ፣ ገንዘብ ሚ/ር ደግሞ ከኢሳፕ ልምድ በመነሳት በአመቻችነት እና አወያይነት ክህሎት ላይ መመሪያ እና ስልጠና ተዘጋጅቶ አንዲሰጥ ያደርጋል።

## 4.7. በማህበራዊ ተጠያቂነት ስራ የመሰረታዊ አገልግሎት ዘርፎች (Basic service sectors) ሚና

- በአዳዲስ ወረዳዎች የሚከናወኑ የማህበራዊ ተጠያቂነት ተግባራት በአሁኑ ወቅት በአገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች፣ በወረዳ ሴክተር ፅ/ቤት እንዲሁም በክልል እና ከተማ

አስተዳደር ደረጃ በስራ ላይ እየዋሉ ካሉት የመንግስት መሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ እቅድ፣ ትግበራ፣ እና ግምገማ ሂደቶች ጋር በተቻለና አቅም በፈቀደ መጠን የተጣጣሙ እንዲሆኑ ይደረጋል። ይህ አሰራር፤ በተለይ ማህበራዊ ተጠያቂነትን ተቋማዊ ከማድረጉ ግብ ጋር በጥብቅ ይያያዛል። በዚህ ረገድ በዳሰሳ ጥናቱ ወቅት ከክልልና ወረዳ የሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ጋር የተፈጠሩ ግንኙነቶችና የተለዩ ምቹ ሁኔታዎች (identified entry points) በመጠቀም በተጠናና በታቀደ ሁኔታ ወደ ስራ መግባት አስፈላጊ በመሆኑ በክልሎች እቅድ ውስጥ ተካቶ ሊቀርብ ይገባል።

- የክልል እና የወረዳ መሰረታዊ አገልግሎት ሴክተሮች ፣የጋራ የድርጊት መርሃ ግብር (JAP)ን ከሴክተር ስትራቴጂያቸው እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ጋር በማጣጣም በበጀት ቀረጻ ወቅት ማካተት ላይ የበለጠ ቀጥተኛ ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ ሚና[4] እንዲጫወቱ በፕሮጀክቱ ድጋፍ ይሰጣል።
- የገንዘብ ሚ/ር ቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት እና የክልል ፋይናንስ ቢሮዎች ከክልል ፕላን ቢሮዎች እና ከአከባቢ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ለክልል እና ለወረዳ መሰረታዊ ሴክተሮች፣ የመንግስት እቅድ እና የበጀት አዘገጃጀትና አመዳደብ ሂደት ላይ ዜጎች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች እንዴት ማካተት እንደሚቻል ስልጠና እንዲዘጋጅ በማድረግ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እንዲሰጥ ያደርጋል።

## 4.8. ለማህበራዊ ተጠያቂነት ትግበራ የአካባቢ ሚዲያዎችን መጠቀም


- የአካባቢ እና የክልል ሚዲያ በሁሉም የማህበራዊ ተጠያቂነት ዑደት ደረጃዎች (SA Cycle) የኢሳፕ አይ.ዲ.ኤ ፕሮጀክት ትግበራን እንዲያግዝ ይደረጋል።[5]
- ይህ ስራ የዜጎችን የአገልግሎት መብቶችና እና ግዴታዎች ላይ ግንዛቤ፣ በትምህርት ቤት ሚዲያዎችን በመጠቀም ማስረፅን፤ ፣የጋራ የድርጊት መርሃ ግብር ዝግጅትና የማፅደቅ ሂደትን (documenting interface meetings and Joint Action Plan (JAP) preparation meetings) እና የአገልግሎት አቅራቢዎችን ከዜጎች ጋር የሚያደርጉትን የግብረ መልስ የውይይት (service provider-user feedback meetings) ክፍለ ጊዜን መቅረፅ እና ዶኩመንት ማድረግን ያካትታል ።
- የማህበራዊ ተጠያቂነት አሰራር ሂደትና ውጤትን፤ እንዲሁም በዜጎች እና በአገልግሎት ሰጪዎች መካከል ያለውን አዲስ የማህበራዊ ተጠያቂነት ግንኙነት (evolving accountability driven social contract between service providers and users) እንዴት እየተፈጠረ እንደሆነ ለማሳየት የሚያስችል የሚዲያ ስትራተጂ እና አሰራር ሂደት የገንዘብ ሚ/ር ቻናል አንድ ፕሮግራሞች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት በዘርፉ ከተሰማሩ የሚዲያ ተቋማትና ባለሙያዎች ጋር በመመካከር ያዘጋጃል።

[4] በተለያዩ የኢሳፕ አይዲኤ ሰልጠናዎች ላይ በተደጋጋሚ እንደቀረበው፤ ቢዚህኛው የፕሮጀክቱ ምእራፍ የመሰረታዊ አገልግሎት ዘርፎች (basic service sectors) ሚና ፤ ቀደም ሲል ከነበረው ’ተባባሪነት’ ወደ ‘ባለቤትነት’ እንደሚሸጋገር ይጠበቃል።

[5] ይህን ስራ በተደራጀ ዘለቄታዊነትን ባረጋገጠ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል፣’ሚዲያ ለማህበራዊ ተጠያቂነት በምን መልክ ሊያገለግል አእንደሚችል የሚያሳይ ሙያዊ ጥናት በቅርቡ ይደረጋል።

### 4.9. የመንግስት መሰረታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ግምገማ መስፈርቶች

- የማህበራዊ ተጥያቂነት ትግበራ ሎደት የሚከትሉትነ አምስት ሂደቶችን ያጠቃልላል[6]፤




- የአገልግሎት ምዘና አመላካቾች (service assessment indicators) የሚዘጋጁት በኢሳፕ ልምድ በሚገባ [7] እንደታየው፤ በዜጎች ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ፍላጎቶች እና የሴክተር አገልግሎት ደረጃዎችን (basic sector service standards) መሰረት በማድረግ ነው።
- የአገልግሎት ምዘና አመላካቾች በተቻለ መጠን ቀላል እና ለዜጎችና አገልግሎት ሰጪዎች ምቹ ሊሆኑ ይገባል። ለዚህም እንደ ተግባራዊነት (manageability)፣ ወጪ ቆጣቢነት (affordability & cost-effectiveness) እና ዘላቂነት (sustainability) ያሉ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።
- የአገልግሎት ምዘና አመላካቾች ከማህበረሰቡ የዕድገት ፍላጎትና ከመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ አቅም ጋር በየጊዜው እያደጉ ሊሄዱና ሊለዋወጡ የሚችሉ ናቸው። በመሆኑም ተገልጋዩ ህብረተሰብ፤ ምዘና ውስጥ ከመግባቱ አስቀድሞ በወቅቱ በስራ ላይ ያሉትን የአገልግሎት አሰጣጥ ደረጃዎች (Sector service delivery standards) ማወቅና መጠቀም ይገባል።

---

[6] የማህበራዊ ተጥያቂነት ትግበራ ሎደት በኢትዮጵያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራም( ESAP-MDTF) ተዘጋጅቶ በስራ ላይ የዋለ ሲሆን በኢሳፕ አይዷኤም ስራው ከመንግስት የበጀት ስሌዳ ጋር ተጣጥሞ ከላይ በቀረበው መልክ የሚቀጥል ይሆናል። በሂደት አፈጻጸሙ እየታየም ማሻሻያ ሊደረግ እንደሚችልም ታሳቢ ተደርጓል።
[7] ኢሳፐ 3 ማኔጅመንት ኤጀንሲ (ESAP3 MA) የወረዳ የማህበራዊ ተጠያቂነት ኤክስፐርት መመሪያ ኤፕሪል 2019
* ይህ የአፈፃፀም ክትትል እስከ ሚቀጥለዉ በጀት አመት ሰኔ ወር ድረስ አመቱን ሙሉ የሚከናወን ነዉ።

## 5. ክትትልና ግምገማ

የፕሮጀክት ክትትል እና ግምገማ ሰፋ ባለ መልኩ የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

- ለገንዘብ ዋጋ (*Value for money*) ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት እና ፕሮጀክቱ የሚያስገኘው ዘላቂ ለውጥ፣(impact) እና
- በስራው ሂደት የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ችግሮችን በመገምገም የእርምት አስተዳደራዊ እርምጃ መውስድና ከሂደቱም ለወደፊት እቅድ ዝግጅትና የተሻለ አፈጻጸም እንዲሁም የፖሊሲ ቀረጻ በግብአትነት መጠቀም (Learning for future improvements and policy inputs ) ናቸው።

የኢሳፕ-አይ.ዲ.ኤ ቁልፍ የግምገማ እና ክትትል ሂደት የሚከተሉትን ማለትም፡-

- የፕሮጀክት ስራዎች የውስጥ አፈፃፀም ግምገማ በመስክ ላይ ያለውን የማህበራዊ ተጠያቂነት ሂደት፣ የሩብ አመት እና ዓመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን እና የልምድ ልውውጥ መድረኮች (internal project review and monitoring) እና
- በገለልተኛ የውጭ አማካሪዎች የሚከናወን የመካከለኛ ጊዜ እና የመጨረሻ የውጭ ተጽእኖ ግምገማ (External mid-term and final project evaluation) ያጠቃልላል።

**በአዳዲስ ወረዳዎች የሚጠበቁ ቁልፍ ውጤቶችና የውጤት መለኪያዎች**

**(ESAP-IDA Key results and Indicators)**

| ተ.ቁ | ቁልፍ ውጤቶች | መለኪያ |
|---|---|---|
| 1 | በወረዳና በክልል ደረጃ ያሉ የመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎችን በመጠቀም የህዝብ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ማሳደግ እንደሚቻል ያላቸው ግንዛቤ ማደግ፤ | • ስልጠና የተሰጣቸው የክልል አገልግሎት ሰጪ ሴክተር ቢሮ አመራሮችና ሰራተኞች ብዛት<br>• ስልጠና የተሰጣቸው የወረዳ አገልግሎት ሰጪ ሴክተር ፅ/ቤት አመራሮችና ሰራተኞች ብዛት |
| 2 | የወረዳና የክልል ምክር ቤቶች የማህበራዊ ተጠያቂነት አሠራሮችንና አቀራረቦችን በመጠቀም የአገልግሎት አቅራቢዎች ለአገልግሎት ተጠቃሚው ህብረተሰብ፤ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ምላሽ ሰጪ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችላቸው ግንዛቤ እና ክህሎት መፈጠር። | • ስልጠና የተሰጣቸው የክልል ም/ቤት ቋሚ ኮሚቴ አባላት ብዛት<br>• ስልጠና የተሰጣቸው የወረዳ ም/ቤት አባላት ብዛት |
| 3 | በየክልሉ እና ከተማ አስተዳደሮች በተመረጡ አዳዲስ ወረዳዎች የማህበራዊ ተጠያቂነት ሙሉ ዑደት (SA Cycle) መተግበር | • ወቅታዊ የሆኑ የሴክተሩን ልዩ የአገልግሎት አሰጣጥ መረጃዎችን እና ደረጃዎችን ለተጠቃሚው ህዝብ ያካፈሉ የመሠረታዊ አገልግሎት ሴክተሮች ብዛት<br>• የማህበራዊ ተጠያቂነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ላይ የተሳተፉ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ቡድኖች እና ዜጎች ብዛት (በጾታ እና በማህበራዊ ቡድን ውክልና በግልጽ የተለየ)<br>• የአገልገሎት አሰጣጥ ግምገማ የተካሄደባቸው አገልግሎት |

| ተ.ቁ | ቁልፍ ውጤቶች | መለኪያ |
| --- | --- | --- |
| | | መስጫ ተቋማት፤ ቀበሌዎችና ወረዳዎች ብዛት<br>• የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያዎችን በመጠቀም በመሠረታዊ የህዝብ አገልግሎቶች ግምገማ ላይ የተሳተፉ የአገልግሎት ተጠቃሚ ቡድኖች/ ዜጎች ብዛት<br>• በአገልግሎት ተጠቃሚ ዜጎች ፍላጎትና በመንግስት ወቅታዊ ሰርቪስ ስታንዳርድ ላይ በመመስረት፤የጋራ የድርጊት መርሃ ግብሮችን Joint Action Plans) የነደፉ ወረዳዎች ብዛት<br>• በሴክተር እቅዳቸው ውስጥ በጋራ የድርጊት መርሃ ግብሮች ላይ የተዘረዘሩ የዜጎችን ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ያካተቱ ወረዳዎችና ሴክተሮች ብዛት<br>• በጋራ አቅዳቸው (JAPs) የተለዩ የዜጎች ፍላጎቶችን መነሻ በማድረግ፤ በቅድመ-በጀት ውይይቶች ላይ የተሳተፉ የማህበራዊ ተጠያቂነት መድረክ (Social Accountability Platform/SAP) አባላትና ያቀረቧቸው ጉዳዮች ብዛት<br>• ከወረዳዎች ከአቅም በላይ የሆኑና በክልል ደረጃ ምላሽ እንዲሰጡ ወደ ክልል ሴክተር ቢሮዎች ከየወረዳው የቀረቡ የአገልግሎት መሻሻል ጥያቄዎች፤ብዛት<br>• የጋራ የድርጊት መርሃ ግብሮች አፈፃፀምን ለመከታተል የተደረጉ ወርሃዊ ስብሰባዎችና፣ በየሶስት ወር የሚደረጉ የመስክ ጉብኝቶች ብዛት<br>• ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በተገቢውየጥራት ደረጃ ተዘጋጅቶ የቀረበ የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ብዛት |
| 4 | በመሠረታዊ የህዝብ አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች የአገልግሎት አሰጣጥ እቅድ፣ ትግበራ እና ክትትል ስርአቶች ውስጥ የማህበራዊ ተጠያቂነት አቀራረቦች እና ዘዴዎች የተካተቱበትና እየተተገበሩ መሄዳቸው | • በየሴክተሩ የተዋቀሩ የማህበራዊ ተጠያቂነት መድረኮች ብዛት እና አይነት<br>• በየሴክተሩ የማህበራዊ ተጠያቂነት አካሄድን እንዲያካትቱ የተከለሱ በስራ ላይ የዋሉ መመሪያዎች ብዛት |
| 5 | የክልል መሰረታዊ አገልግሎት ሴክተር ቢሮዎች ለወረዳ/ክፍለ ከተማ አገልግሎት ሰጭ ሴክተር መ/ቤቶች የዜጎችን አገልግሎት ቅድሚያና ጥያቄዎችን በብቃት ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት የሚሰጧቸው የዕቅድ፣ የትግበራ፣ የክትትልና የፖሊሲ ድጋፍ ውጤታማነት። | • የመንግስት አገልግሎት ሰጪ ሴክተሮች ቀደም ሲል ከነበረው በተሻለ ለዜጎች አገልግሎት ጥያቄ ምላሽ እየሰጡ እንደሆነ የሚያረጋግጥ የዳሰሳ ጥናት ሰነድ |